የኮንስትራክሽን ሥራ ድርጅቶች ምዝገባና ሰርተፍኬሽን ዳይሬክቶሬት

የንብረት አቻ ግመታ፣ የፕሮጀክት መጠን፣ የመሳሪያ እና የሰው ኃይል መስፈርት፣

ኢትዮጵያዊ ወይም ትውልደ ኢትዮጵያዊ ዜግነት ላላቸው አመልካቾች

ሀ) የታደሰ የቀበሌ መታወቂያ /መንጃ ፍቃድ፣ ፓስፖርት ... ዋናውን እና ኮፒ፣

ለ) ሊያወጡ በፈለጉት ደረጃ የሚጠይቀውን የባለሙያ ምስክር ወረቀት ምስክር ወረቀት ሰጪው እንዲሁም የድርጅቱ ተቀጣሪ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ የቅጥር ውል ዋናውን፣

ሐ) ለእድሳት/ ለእድገት ለሚመጡ አማካሪዎች የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት፣

መ) አመልካቹ የንግድ ማህበር ከሆነ ህጋዊ የመመስረቻ ፅሁፍና መተዳደሪያ ደንብ ዋናውን እና ኮፒ፣

ሠ) የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር (Tin Number)፣

የአማካሪዎች ደረጃ፣ ፕሮጀክት መጠን እና የሰው ኃይል መስፈርት

1. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 17 ከሀ እስከ ሠ መሠረት በተገለፁት ዘርፎች የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማግኘት በአንዱ ማመልከት የሚችል ሲሆን የሰው ሃይልንና የፕሮጀክት አፈጻጸም መስፈርቶችን መሠረት በማድረግ ከተዘረዘሩት ደረጃዎች ውስጥ በአንዱ ወይም ከአንድ በላይ በሆኑ ዘርፎች ሊያመለክቱ ይችላሉ።
2. በዚህ መመሪያ መሠረት አንድ አመልካች በአማካሪነት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማግኘት ላመለከተበት ምድብና ደረጃ የሚያስፈልጉ ባለሙያዎችንና የፕሮጀክት አፈጻጸም ማስረጃ ማቅረብ አለበት።
3. ማንኛውም አማካሪ የብቃት ማረጋገጫ ለማውጣት የድርጅቱ ስራ አስኪያጅ የፕራክቲሲንግ ፕሮፌሽናል የምስክር ወረቀት ሊኖረው የሚገባ ሲሆን የድርጅቱ ስራ አስኪያጅ ተቀጣሪ ወይንም ባለቤት መሆን ይችላል። በስራ አስኪያጅነት የሚቀርበው ባለሙያ፣ ሙሉ በሙሉ የድርጅቱ ባለቤት ካልሆነ ቢያንስ እስከ 30 በመቶ የድርጅቱ የሀብት ድርሻ (Share) ሊኖረው ይገባል።
4. አማካሪዎች የሚያቀርቡትን ፕሮጀክት የሚገልፅ የመልካም ስራ አፈፃፀም መግለጫ ማያያዝ የሚጠበቅባቸው ሲሆን የሚፃፈው የመልካም ስራ አፈፃፀምም የፕሮጀክቱን አይነት፣ ፕሮጀክቱ የሚከናወንበትን ስፍራ፣ ክልል፣ ከተማ፣ የስራውን ስፋት (በገንዘብ መጠን)፣ የስራው የቆይታ ጊዜ፣ የደብዳቤ ቀን እና ቁጥር፣ የአሰሪው አካል ፊርማና ቲተር እንዲሁም የድርጅቱን ማህተምና አድራሻ የያዘ መሆን አለበት።

1. አመልካቾች የሚያመለክቱበት የኮንስትራክሽን አማካሪነት መደብ ከተዘረዘሩት መደቦች ውስጥ ከሌለ እንደአስፈላጊነቱ ረቂቅ መስፈርት በማዘጋጀት ስራ ላይ ከመዋሉ በፊት በሚመለከተው አካል እንዲፀድቅ የሚደረግ ሆኖ እስከዚያው ግን በንግድ ሚኒስቴር ባልተካተቱ የንግድ ዘርፎች ፈቃድ እየተስተናገዱ ስርአቱ ሲዘረጋ ወደ መደበኛው ስርአት እንዲገቡ የሚደረግ ይሆናል፡፡
2. የአማካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ለማውጣት ሴት/ አካል ጉዳተኛ ከሆነ / ች ወይም ስራ አስኪያጇ ሴት/ አካል ጉዳተኛ ከሆነ / ች ወይም ማህበሩ ውስጥ ካሉት አብላጫው ሴቶች / አካል ጉዳተኞች ከሆኑ ለየደረጃው የሚጠየቀው የጠቅላላ ፕሮጀክት ብር መጠን በ 15 ፐርሰንት የሚቀንስ ይሆናል፡፡
3. በአማካሪነት የሚመዘገቡ ድርጅቶች ከዕዝል (6 እስከ ዕዝል 13) የተዘረዘሩትን መስፈርቶች ማሟላት ይጠበቅባቸዋል፡፡

ልዩ ሁኔታ

የህንጻ አማካሪ፣የሃይዌይ አማካሪና የመሳሰሉት አጠቃላይ የማማከር አገልግሎት ለመስራት የሚሰጡት የምዝገባ ወይም የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቶችን በተመለከተ የተቀመጡትን መስፈርቶች ላሟሉ ድርጅቶች መስጠቱ እንደተጠበቀ ሆኖ የተለያዩ የባለሙያ ድርጅቶች በመግባቢያ ሰነድ አብረው ለመስራት የፈጠሩትን ስምምነት በማቅረብ መስፈርቶቹን የሚያሟሉ ከሆነ አጠቃላይ የማማከር አገልግሎት መስጠት እንዲችሉ በተለየ ሁኔታ ሊፈቀድላቸው ይችላል።

በኮንስትራክሽን የማማከር አገልግሎት ላይ በቂ ልምድ ያላቸውና ከቀጣሪዎቻቸው (ከመንግስታዊ ተቋም፤ መንግስታዊ ካልሆነ ድርጅት ወይም ከግል ድርጅቶች) መልቀቂያ የሚያቀርቡ ወይም የዩኒቨርሲቲ መምህራን አማካሪ ለመሆን ፍላጎት ያላቸው ምንም አይነት መስፈርቶች በቅድሚያ ማሟላት ሳያስፈልጋቸው ለሚከተሉት ደረጃዎች የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ማግኘት ይችላሉ። ይሁንና ለሴት ባለሙያዎች ወይም ለአካል ጉዳተኞች የሚጠየቀው የአገልግሎት ልምድ በሁለት (2) ዓመት ዝቅ ያለ ይሆናል።

1. ፕሮፌሽናል ባለሙያ ከዲግሪ በኋላ 8 ዓመት አገልግሎት ላላቸው በደረጃ III ከሰሩበት የሙያ መስክ ተዛማጅ በሆነው የአማካሪ መደቦች በአንዱ፤
2. ፕራክቲሲንግ ፕሮፌሽናል ባለሙያ ከዲግሪ በኋላ 6 ዓመት አገልግሎት ላላቸው በደረጃ III ከሰሩበት የሙያ መስክ ተዛማጅ በሆነው የአማካሪ መደቦች በአንዱ፤
3. ፕራክቲሲንግ ፕሮፌሽናል ባለሙያ ከዲግሪ በኋላ 8 ዓመት አገልግሎት ላላቸው ባለሙያዎች በትንሹ ሶስት ሆነው የተደራጁና ተመጋጋቢ የሆነ የት/ት መስክ ስፔሻላይዜሽን ያላቸው በደረጃ II፤

የንብረት አቻ ግመታ (Asset Valuation) አማካሪ

ተ. ቁ	ለየደረጃው የሚያስፈልገው የባለሙያ አይነት	ደረጃ
		5
1	ፕሮፌሽናል መሀንዲስ (ሲቪል ወይም ተያያዥ የት/ት መስክ) ፤	1
2	ፕሮፌሽናል መካኒካል ኢንጂነር (Professional Mechanical Engineer) ፤	1
3	ፕሮፌሽናል ኳንቲቲ ሰርቬየር (Professional Quantity Surveyor)	2
5	ምሩቅ መሀንዲስ (Graduate Engineer)፤	1
6	አካውንታንት Accountant (IFRS certified) እና 3 ዓመት የስራ ልምድ ያለው/ላት፤	1
	ድምር	6

የአገልግሎት ክፍያ መጠን

የባንክ አካውንት፡ 1000273073737

ደረጃ	ስራ ተቋራጭ	አማካሪ	የውጭ ዜጎች
	አዲስ፤ዕድሳት ፤ዕድገት	አዲስ፤ዕድሳት ፤ዕድገት	አዲስ፤ዕድሳት ፤ዕድገት
1	1350.00	1400.00	200 ዶላር
2	1300.00	1300.00	
3	1200.00	1200.00	
4	1100.00	1100.00	
5	1000.00	1000.00	
6	1000.00	1000.00	
7	900.00	900.00	
8	900.00	900.00	
9	850.00	850.00	
10	850.00	850.00	

የመጫረቻ ዋጋ (የፕሮጀክቱ አጠቃላይ የግንባታ ዋጋ) በብር

የልዩ ስራ ተቋራጮች ከፍተኛ የመጫረቻ ዋጋ በብር

ደረጃ	የፕሪ ቴንሽኒግ ስራ ሚሊየን ብር	በፖስት ቴንሽኒንግ ስራ ሚሊየን ብር	የመሬት ገጽታ ማስዋብ ስራ ሚሊየን ብር	የመሠረት ስራዎች ስራ ተቋራጭ ሚሊየን ብር	የመንገድ ላይ የትራፊክ ደህንነት መቆጣጠሪያ ምልክት ሥራ
8	ወሰን ለዉም	ወሰን ለዉም	ወሰን ለዉም	ወሰን ለዉም	ወሰን ለዉም
9	እስከ 100	እስከ 15	እስከ 10	እስከ 100	እስከ 80
10	እስከ 40	እስከ 10	እስከ 4	እስከ 50	እስከ 30

አማካሪዎች ሚሳተፉበት ፕሮጀክት አጠቃላይ የፕሮጀክት ግንባታ ዋጋ በብር

ተ.ቁ	ምድብ	ደረጃ / የፕሮጀክት ዋጋ በሚሊዮን ብር			
		1	2	3	4
1	የህንፃ አማካሪ	ወሰን የለዉም	እስከ 500	እስከ 150	እስከ 85
2	የአርክቴክቶች አማካሪ	ወሰን የለዉም	እስከ 400	እስከ 120	እስከ 60
3	የመሀንደሶች አማካሪ	ወሰን የለዉም	እስከ 750	እስከ 350	እስከ 150
4	የሀይዌይና ድልድይ አማካሪ	ወሰን የለዉም	እስከ 850	እስከ 500	እስከ 250
5	የኮንስትራክሽን ማኔጅመንት አማካሪ	ወሰን የለዉም	እስከ 850	እስከ 500	እስከ 250
6	የከተማ ፕላን አማካሪ	(የህዝብ ብዛት 100001 በላይ ያላቸው)	(የህዝብ ብዛት ከ50001- 100000 በላይ ያላቸው)	(የህዝብ ብዛት ከከ20000-50000 በላይ ያላቸው)	(የህዝብ ብዛት እስከ 20000 ያላቸው)

የልዩ አማካሪዎች ከፍተኛ የጨረታ ዋጋ

ተ.ቁ	ምድብ	ደረጃ / የመጫረቻ ዋጋ በሚሊየን ብር			
		5	6	7	8
1	የአፈር ምርመራ አማካሪ	ከ 3 ሚሊየን በላይ (ወሰን የለዉም	ከ1.5 እስከ 3 ሚሊየን (አስከ 30 ወለል)	ከ 500 ሺህ እስከ 1.5 ሚሊየን (አስከ 15 ወለል)	ከ 500 ሺ በታች (አስከ 5 ወለል)
2	የንብረት አቻ ግመታ (Asset Evaluation) አማካሪ	----	---	----	----

 # እናሳካለን !

“ውጤታማ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ለኢትዮጵያ ብልፅግና”

የኮንስትራክሽን ስራዎች ተቆጣጣሪ ባለስልጣን